ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያውያን ትብብር ለፍትኅ
Global United Ethiopians Movement for Justice

‘

ለኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር

ዶ/ር አብይ አህመድ

አዲስ አበባ

# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ፣ የአማራ ነገድ ተወላጆችና ሌሎች ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ላይ ቄሮ የተባለው አክራሪዉ አሸባሪ ቡድን ያደረሰውን ዘግናኝ፣ አሰቃቂ ፣ አረመኔያዊና ኢሰበአዊ ጭፍጨፋ በጽኑ እናወግዛለን ። ወንጀለኞች በአስቸኳይ ለፍርድ እንዲቀርቡ አጥብቀን እንጠይቃለን ።

ከሰሞኑ በሐገራችን ኢትዮጵያ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በተለያዩ ከተሞችና የገጠር መንደሮች ይኖሩ በነበሩ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች፡ ወንጌላውያን፡ እስላሞች፡ በብሄር አማሮች ላይ ያነጣጠረ እንዲሁም የጋሞ ፣ የስልጤ ፣ የዶርዜ ብሄር አባላት የሆኑ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ላይ በአቶ ጃዋር መሐመድ አነሳሽነት በእርሱ የሚመራዉ አክራሪዉ ቄሮ በተባለው አረመኔያዊና አሸባሪ ቡድን እጅግ ዘግናኝ አሰቃቂና ፍጹም ጭካኔ በተመላበት ሁኔታ መንግስት ባመነዉ ፹፮ የሚደርሱ ነገር ግን ቁጥሩ ከዚያም በላይ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ተጨፍጭፈዋል ። ከአራት መቶ በላይ መቁሰልና የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል ። በንብረት ላይም ግምቱ ያልታወቀ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል ።

ይህ ኢሰብአዊና አረመኔያዊ ጭፍጨፋ ህጻናትን ፣ ነፍሰ ጡር ሴቶችን ፣ የአልጋ ቁራኛ አረጋውያንን ፣ ህሙማን ሆስፒታል በተኙበት፡ በሕግ ጥላ ስር የነበሩ  እስረኞችን ፡ የሃይማኖት አባቶችን ፣ የወንጌል አስተማሪዎችን ሁሉ በጭካኔ የጨፈጨፈ ነበር ። ይህ አረመኔ አሸባሪ ቡድን የ፹ ዓመት የአልጋ ቁራኛ የነበሩ አረጋዊ አባት እንኳን ርህራሄ በሌለው ሁኔታ ሰውነታቸውን ቆራርጦ ገድሏል ። አክራሪዉ አሸባሪ ቄሮ ይህን የሽብር ተግባር የፈጸመው በሜጫ አንገታቸውን እየቀላ በስለት እየወጋ በዱላና በድንጋይ እንደ አውሬ እየቀጠቀጠ እጅና እግራቸውን እየቆረጠ ፣ የሴቶች ጡት እየቆረጠ፣ የወንዶችን ብልት እየሰለበ እንዲሁም መላ ሰውነታቸውን እየከታተፈ ለመናገርና ለማመን ፈጽሞ በሚዘገንን አረመኔያዊና ኢሰብአዊ በሆነ ሁኔታ ነው ። ይህ አይነት አረመኔያዊ ጭፍጨፋ እንኳን ሐገረ እግዝዚአብሄር በሆነችው ሐገራችን ኢትዮጵያ ይቅርና በየትኛውም የሽብር ጥቃት በተፈጸመባቸው ሐገሮች ተሰምቶም ተዘግቦም አያውቅም ።

በ፳፩ኛው ክፍለ ዘመን የሰው ልጅ ከራሱ አልፎ ለእንስሳ ሕይወትና አያያዝ ከፍተኛ ሰብአዊ ርህራሄ እያሳየ ባለበት ጊዜ በአንጻሩ በሐገራችን ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር ፍጡር የሆነ ሰው በእንደዚህ አይነት ዘግናኝና አረመኔያዊ ጭፍጨፋ መገደሉ እጅግ አሳዝኖናል ፣ አስቆጥቶናልም ። ለዚህ ሁሉ አሰቃቂ ኢሰብአዊ ጭፍጨፋና ከ፹፮ በላይ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በዘግናኝ ሁኔታ መገደል ከሶስት መቶ በላይ ለሚሆኑ የተለያየ አካል ጉዳት መድረስ እንዲሁም ግምቱ ገና


POBOX 3005 Tucker GA. 30085
mailto:guethio.4justice@gmail.com

ላልታወቀ የሐብትና ንብረት ውድመት ብሎም ለኢትዮጵያውያን በሙሉ ድንጋጤና ጭንቀት መንስዔ የሆነው የአቶ ጃዋር መሐመድ ተከብቤያለሁ ድረሱልኝ የሚል ሰይጣናዊ ጥሪ በማስተላለፉ ምክንያት ነው ። ከዚህም የተነሳ ጃዋርና ግብረ አበሮቹ  ለዚህ ሁሉ ጭፍጨፋና የዘር ማጥፋት ወንጀል ዋና ተጠያቂዎች ናቸው።

በጣም የሚገርመው ነገር ደግሞ ይህ ሁሉ አረመኔያዊ ጭፍጨፋ በወገኖቻችን ላይ ሲፈጸም ኢትዮጵያን እመራለሁ የሚለው የፌዴራል መንግሥት፣ የኦሮሚያ ክልል አመራር፣ የከተሞች ከንቲባዎችና ፡ በጠቅላላ የጸጥታ መዋቅሩ ጭፍጨፋውን ለመከላከል ምንም አይነት እርምጃ አለመውሰዳቸዉ ነው ። አንዳንድ በአሸባሪውች ጥቃት ቆስለው በህይወት የተረፉ ወገኖቻችን እንደገለጹት ከሆነ የኦሮሚያ ፖሊስ ፣ አድማ በታኝ ፣ ልዩ ኃይል ቆሞ እያየ ከተጠቂዎች እርዳታ ቢጠየቅም ምንም አይነት ድጋፍ ለማድረግ ፈቃደኛ አለመሆኑ ነው ።

መንግሥት ቁጥር አንድ ተግባሩ የሐገርና የዜጎችን ደህንነት መጠበቅ ሆኖ እያለ ለምንድነው ዝም ብሎ የተመለከተው?  የሐገር ደህንነትና የጸጥታ መዋቅሩ ዋና ስራው እንደዚህ አይነት ከፍተኛ ወንጀሎች ገና ሲጠነሰሱና አንዳንድ ምልክቶች ሲታዩ ማምከን አይደለም ወይ ? ጭፍጨፋው እንደተጀመረስ ለምን ፖሊስ ልዩ ኃይል በአስቸኳይ እንዲያስቆመው አልሆነም ? ፖሊስ ለአሸባሪዎች ወግኖ ሃላፊነቱን መወጣት ካልፈለገ የሐገሪቱ መከላከያ ሰራዊት ለምን ሁለት ቀን ዘግይቶ እንዲገባ ተደረገ ? ወይንስ ሆን ተብሎ የሃይማኖትና የዘር ማጽዳት ጭፍጨፋ ነው የተካሄደው ? ይህ ሁኔታ ሁሉንም የሚመለከታቸዉ የመንግስት አካላት ከተጠያቂነት አያድናቸዉም ።

ሌላው ዋነኛ ጉዳይ ደግሞ መንግሥት የተከሰተው ግጭት ነበር እያለ በተደጋጋሚ በመግለጽ ላይ ቢሆንም እውነታው ግን ጭፍጨፋ እንጂ ፈጽሞ ግጭት አይደለም ። ግጭት ለመባል ሁለት ኃይሎች ጎራ ይዘው ሲፋለሙ ነው ። የሆነው ግን በአቶ ጃዋር መሐመድና ግብረ አበሮቹ የተነሳሳው ወይንም ትእዛዝ የተቀበለው ፅንፈኛዉ ቄሮ የተባለው አሸባሪ ቡድን ወገኖቻችንን በሃይማኖታቸውና ብሄራቸው ለይቶ ነው ጭካኔያዊ ጭፍጨፋ ያደረሰባቸው ።

ይህ አረመኔያዊ ጭፍጨፋ በአቶ ጃዋር መሐመድ ብቻ ሳይሆን በሕውሃትና በኦነግ ትብብር እንዲሁም የኢትዮጵያ ጥንተ ጠላት በሆኑ የውጪ ኃይሎች የተቀነባበረ ለመሆኑ ብዙ አመላካች ሁኔታወች አሉ ። ይህ ጭፍጨፋ ተራ የሽብር ወንጀል ሳይሆን የሰው ዘርን ከማጥፋት ጋር በቀጥታ የተያያዘ ስለሆነ በዓለም አቀፍ ሕግ መሰረት በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት የሚያስከስስም ይሆናል ። ቢዘገይም እንኳን ሁሉም በየደረጃው የሚጠየቁበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም ። ለማስታወስ ያህል በደርግ ስልጣን ዘመን የደርግ አባል የነበረው መቶ አለቃ እሸቱ አለሙ በቀድሞዉ የጎጃም ክፍለ ሐገር በደብረ ማርቆስ ፣ በሞጣ ፣ በአገው ምድር ፣ ቆላ ደጋ ዳሞት ወዘተ ከተሞች የነበሩ የኢሕአፓ አባላትን በእብሪተኝነት ያለምንም ፍርድ ሂደት በራሱ ስልጣን ከየእስር ቤቱ እያስወጣ ብዙ ወጣቶችንና ምሁራንን በመረሸኑ ከብዙ ክትትል በኋላ ወንጀሉ ተረጋግጦ ከደርግ ውድቀት በኋላ በስደት በሚኖርበት ሆላንድ ውስጥ ወንጀሉን ከፈጸመ ከ፴ ዓመት በኋላ የእድሜ ልክ እስራት ተፈርዶበት ወህኒ ቤት ውስጥ ይገኛል ። ይህ ሁኔታ አሁን ባለጊዜ ነን ብለው ወንጀል ለሚፈጽሙ የመንግስት ሃላፊዎች፣ የወንጀል ተባባሪ ለሚሆኑ ወይንም ከለላ ለሚሰጡ ሁሉ ከወንጀለኛው ጋር እንደመተባበር ስለሚቆጠር ከተጠያቂነት እንደማይድኑ በመገንዘብ ከዚህ በኋላ ከዚህ መሰል አስነዋሪና ህገወጥ ተግባራቸዉ በመማር ህግን በስርአት ማስከበር እንደሚገባቸው ማወቅ ይኖርባቸዋል ።


POBOX 3005 Tucker GA. 30085
mailto:guethio.4justice@gmail.com

እንደዚህ አይነት ዘግናኝና አረመኔያዊ ጭፍጨፋ ያቀነባበሩና የፈጸሙ በወንጀላቸው እንዲጠየቁ እንዲሁም በሐገራችን ኢትዮጵያም ሆነ በየትኛውም የዓለም ክፍል ዳግም እንዳይከሰት ለማድረግ ለኢትዮጵያ መንግሥትና ለዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ የሚከተሉትን ጥያቄዎች እናቀርባለን ።

ለኢትዮጵያ መንግሥት

፩ኛ ይህንን ጭፍጨፋ በማነሳሳትም ሆነ ወይንም ድብቅ ትዕዛዝ በመስጠት የሽብር ድርጊቱ እንዲፈጸምና ከ፹፮ በላይ ኢትዮጵያውያን በአሰቃቂ ሁኔታ እንዲገደሉና በመቶዎች የሚቆጠሩ የተለያየ የአካል ጉዳት እንዲደርስባቸውና ሃብት ንብረታቸው እንዲወድም ምክንያት የሆነው አቶ ጃዋር መሐመድና ግብረ አበሮቹን ለፍርድ እንዲያቀርብ አጥብቀን እንጠይቃለን ።

፪ኛ ፅንፈኛዉ ቄሮ የተባለው አሸባሪ ቡድን ይህንን አረመኔያዊ ጭፍጨፋ በማካሄዱ ወንጀሉን የፈጸሙት ተለይተው ለፍርድ እንዲቀርቡ ፣ እንዲሁም የፅንፈኛዉ ቄሮ አደረጃጀት በሕግ እንዲታገድ እንጠይቃለን ።

፫ኛ አረመኔያዊ ጭፍጨፋ በፅንፈኛ አሸባሪ ቄሮ ቡድኖች ሲፈጸም እያዩ መከላከል ያላደረጉ የኦሮሚያ የፖሊስ ፣ የአድማ ብተናና የደሕንነት አባላት ተለይተው ለፍርድ እንዲቀርቡ እንጠይቃለን ።

፬ኛ ይህ ጭፍጨፋ እንዲካሄድ ለዓመታት ሰፊ ቅስቀሳ ሲያካሂድ የቆየውና እያካሄደም ያለው ከሩዋንዳው ሚሌኮሊንስ የሬዲዮ ጣቢያ ጋር በጣም የሚመሳሰለው የኦሮሚያ ሚዲያ ኔትወርክ እንዲዘጋ አጥብቀን እንጠይቃለን ። በጣቢያው እየቀረቡ ሕዝብን ከሕዝብ የሚያጋጭ ቅስቀሳ ሲያካሂዱ የነበሩ ሁሉ በሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑ እንጠይቃለን ።

፭ኛ የኦሮሚያ ምክትል ፕሬዘዳንት አቶ ሺመልስ አብዲሳ ይህንን ጭፍጨፋ ያስነሳው አቶ ጃዋር መሐመድ መሆኑን እያወቁ ወንጀለኛ ስለሆነ ለሕግ መቅረብ አለበት ሳይሆን ወንድማችን ነው እንዲያውም የተጠናከረ ጥበቃ ይደረግለታል ማለታቸው ጭፍጨፋውን ለሚያካሂዱ አረመኔዎች አይዟችሁ የጀመራችሁትን ቀጥሉበት የሚመስል መልዕክት ያዘለ በመሆኑና ጭፍጨፋው ቢቀጥልም ለማውገዝም ሆነ ለማስቆም ምንም ጥረት ባለማድረጋቸው በሕግ እንዲጠየቁ እንጠይቃለን ።

፮ኛ የኦሮሚያ የሕዝብ ደህንነት ሃላፊዎች ፣ የፖሊስ አዛዦች ፣ የዞን ፣ የወረዳና የቀበሌ አመራሮች ጭፍጨፋውን ከመድረሱ በፊት ባለመከላከላቸውና ከተጀመረ በኋም በፍጥነት ባለማስቆማቸው በሕግ እንዲጠየቁ እንጠይቃለን ።

፯ኛ በባሌ ሮቤ ከተማ ያባገዳ መሪዎች ቀጣይ የዘር ማጽዳት በኦርቶዶክስ አማኞች ፣ አማሮችና ኦሮሞ ባልሆኑት የአካባቢው ነዋሪዎች ላይ በማወጃቸው በሕግ እንዲጠየቁ እንጠይቃለን ። አካባቢውም በመከላከያ ሰራዊት ጥበቃ ውስጥ እንዲሆን እንጠይቃለን ።

፰ኛ የኢፌድሪ የሕዝብ ደህንነት ሃላፊ ይህ ጭፍጨፋ እንዳይካሄድ የሚያስችል መረጃ በመሰብሰብ ሕዝቡን ከዕልቂት ለመታደግ ባለመቻሉና ከተጀመረም በኋላ ለማስቆም ይህ ነው የሚባል ጥረት ሲያደርግ ባለመታየቱ በሕግ እንዲጠየቅ እንጠይቃለን



ሥሙ በግልጽ እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ ውስጥ ፍትህ እንዲሰፍን የሚሰራ ፤ ከዚህ በፊት ዛሬ ወይም ነገ ፍትህ ሲጓደል ለኢትዮጵያ መንግሥትና ህዝብ እንዲሁም ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የማሳየት እና የተጓደለው ፍትኅ አስተማማኝ በሆነ መልኩ እንዲሟላ የሚሰራ አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ነው ።
POBOX 3005 Tucker GA. 30085
mailto:guethio.4justice@gmail.com

፱ኛ የኢፌድሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶክተር አብይ አሕመድ ይህ ጭፍጨፋ መካሄዱን እንዳወቁ ለማስቆም የፌዴራል ፖሊስ ፣ የደህንነት አባላትና የመከላከያ ሰራዊት በአስቸኳይ እንዲገባ ትዕዛዝ ባለመስጠታቸው በሕግ እንዲጠየቁ እንጠይቃለን ።

፲ኛ ለሞቱት ቤተሰቦች ተገቢው ካሳ መንግሥት እንዲሰጣቸው እንጠይቃለን ።

፲፩ኛ በእዚህ አሰቃቂ ወንጀል አካላቸው የጎደለ ሕክምና እንዲያገኙ መቋቋሚያም እንዲሰጣቸው እንዲሁም ቤት ንብረታቸው የንግድ ቤቶቻቸው ለወደሙባቸው ሁሉ ተገቢው ምትክ እንዲሰጣቸው እንጠይቃለን ።

፲፪ኛ ከጨፍጫፊውና አሸባሪው ፅንፈኛዉ የቄሮ ገዳይ ቡድን እራሳቸውን በመከላከል ላይ የነበሩ ወጣቶችን ፖሊስ እንደ ወንጀለኛ በጅምላ አስሯቸው ስለሚገኝ ከወንጀለኞች ጋር ተደምረው መታሰራቸው አግባብ ስላልሆነ በአስቸኳይ እንዲፈቱ እንጠይቃለን ።

፲፫ኛ የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለዚህ ሁሉ የማያባራ እልቂት ዋነኛ ምክንያቱ አሁን ያለው ዜጎችን በእኩልነት የማያይ ሕገ መንግሥትና ጎሳና ቋንቋን መሰረት አድርጎ የተቋቋመው የፌዴራል የክልል አወቃቀሩ ስለሆነ ባስቸኳይ ይህ ሕገ መንግሥት ታግዶ ሌላ ሕገ መንግሥት ተረቆ በማጽደቅ በእውነተኛና ተቀባይነት ባላቸው የፌዴራሊዝም መርሆዎች ላይ የተመሰረተ ፌዴራላዊ የክፍለ ግዛት አወቃቀር እንዲመሰርት እንዲያደርግ እንጠይቃለን ።

ለዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ

፩ኛ አቶ ጃዋር መሐመድና ተባባሪዎቹ የዓለም አቀፍ ሽብርተኞች ከሚፈጽሙት እጅግ የከፋ ኢሰብአዊ የሆነ የዘር ማጽዳትና በሃይማኖት ላይ ያነጣጠረ ከፍተኛ ወንጀል ስለፈጸሙ የኢትዮጵያ መንግሥት ሄግ ለሚገኘው የዓለም አቀፉ ፍርድ ቤት አሳልፎ እንዲሰጥ ጫና እንዲያደርግበት እንጠይቃለን ።

፪ኛ አቶ ጃዋር መሐመድ የዩናይትድ ስቴትስ ዜጋ ስለሆነ አሜሪካ ይህ ከባድ ወንጀል የፈጸመ ዜጋዋ በኢትዮጵያ መንግሥት ተይዞ ለአሜሪካ ተላልፎ እንዲሰጥና በአሜሪካን ሕግ እንዲጠየቅ በጥብቅ እንጠይቃለን ። ኦሮሚያ ሚዲያ ኔትዎርክ የተባለው ሚዲያውም ከአሜሪካም ሆነ ከየትም እንዳይተላለፍ እንዲታገድ እንጠይቃለን ።

፫ኛ የኢትዮጵያ መንግሥት ጭፍጨፋው ከመጀመሩ በፊት ባለመከላከሉ ከተጀመረ በኋላም በቶሎ ባለማስቆሙ ብሎም የሽብር ድርጊቱ ዋና ተዋናይ የሆነውን አቶ ጃዋር መሐመድን ወደ ፍርድ ቤት እንደማቅረብ ወደ ሽምግልናና እርስበርስ የመታረቅ ሂደት ላይ በመሆኑ ይህ ድርጊቱ ከወንጀሉ ጋር ተባባሪ ስለሚያስመስለው ዓለም አቀፍ ማሕበረሰቡ በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ተገቢውን ጫና በማድረግ አቶ ጃዋርንና ተባባሪዎቹን በቁጥጥር ስር እንዲያውል አጥብቀን እንጠይቃለን ።

፬ኛ ይህ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮችንና የአማራ ነገድ የማጥፋት ብሎም በእስልምና እምነት ተከታዮችና ሌሎች ወገኖች ላይ የደረሰዉ የሽብር ወንጀል በገለልተኛ ወገን መጣራት ስላለበት የተባበሩት መንግሥታት መርማሪ ቡድን ገብቶ እንዲያጣራ አጥብቀን እንጠይቃለን ።


POBOX 3005 Tucker GA. 30085
mailto:guethio.4justice@gmail.com

፭ኛ የዶክተር አብይ መንግሥት ስልጣን ከያዘ በኋላ ዘርና ሃይማኖትን ላይ ያተኮሩ ጭፍጨፋዎች ሁሉ ለምሳሌ የቡራዩ ፣ የኬሚሴና አጣዬ ፣ በሲዳማ የተካሄዱ ጭፍጨፋዎች ሁሉ ፣ በሰኔ ፲፭ በአማራ ክልል አመራሮች ላይና በሁለት የመከላከያ ጄኔራሎች ላይ የደረሰው ግድያ እንዲሁም የኢንጂነር ስመኘው ሚስጥራዊ ሞትና ከሃምሳ በላይ አብያተ ክርስቲያናትና መስጊዶች መቃጠል በዓለም አቀፍ ገለልተኛ አጣሪ ቡድን እንዲጣራ እንጠይቃለን ።

፮ኛ አሁን ከደረሰዉ እጅግ የባሰ ሃይማኖትንና ብሄርን መሰረት ያደረገ ጭፍጨፋ ሊካሄድ ስለሚችል የተባበሩት መንግሥታት በኦሮሚያ ክልል የሰላም አስከባሪ ኃይል እንዲያሰማራ እንጠይቃለን ።

ኢትዮጵያ የደረሰባት ቀዉስ እጅግ አደገኛ ስለሆነ ከሩዋንዳ የከፋ ዕልቂት እንዳይፈፀም፣ ብሎም ለቀጠናዉ አገሮች ብቻም ሳይሆን ለአለም ሰላምና ጸጥታ መደፍረስም ሆነ የንግድ ዝዉዉር መታወክ ምክንያት ስለሚሆንና እንዲሁም ለሚሊዮኖች ስደት ስለሚዳርግ አስቸኳይ መፍትሄ እንደሚሻ የኢትዮጵያ መንግስትንና የአለም አቀፉን ማህበረሰብ ልናስጠነቅቅ  እንወዳለን።

የኢትዮጵያ ህዝብ በገጠር በከተማ የሚኖረዉ በየሰፈሩ ተደራጅቶ ራሱን ፣ ቤተሰቡን ፣ የሃይማኖት ተቋማትን ፣ የራሱንና የአገር ሀብት እንዲጠብቅ ወገናዊ ጥሪ እናቀርባለን ።

ግልባጭ :-

ለኢፌዲሪ ፕሬዜዳንት

ወ/ሮ ሣህለወርቅ ዘዉዴ

ለኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር

አቶ ደመቀ መኮንን

ለኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ

አቶ ታገሰ ጫፎ

ለኢትዮጵያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዘዳንት

ወ/ሮ መአዛ አሸናፊ

ለኢትዮድያ ጠቅላይ አቃቢ ሕግ ምንስቴር

አቶ ብርሃኑ ፀጋየ

ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሽነር

ዶ/ር ዳንኤል በቀለ


POBOX 3005 Tucker GA. 30085
mailto:guethio.4justice@gmail.com

ለአማራ ክልላዊ መንግሥት  ርዕሰ መስተዳደር

አቶ ተመስገን ጥሩነህ

ለኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳደር

አቶ ሺመልስ አብዲሳ

በአሜሪካ የኢትዮጵያ አምባስደር

አቶ ፍጹም አረጋ

ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጉባኤ

አቶ ቢኒያም አባተ

አዲስ አበባ

ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ማኅበር ዋና ዳይሬክተር

አቶ ያሬድ ኃይለማርያም

ብረሰልስና ጄኔቫ


POBOX 3005 Tucker GA. 30085
mailto:guethio.4justice@gmail.com